# እኔን ግራ ገባኝ!

ከ አዜብ ተስፋዬ (ስዊዘርላንድ)

ሰሞኑን በሀገራችን ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ዙርያ ብዙ ሲባል ብዙ ሲጻፍ ሰንብቷል፡ ቀነስ ብሎ እንደሆነ እንጂ አላቆመም:: ከሀገራችን ርቀን ብንኖርም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ኢትዮጵያ በልባችን ውስጥ ልዩ ስፍራ ይዛ አብራን ትዞራለች:: በፖለቲካ ጎራ ልናደራጃችሁ ነው! ልንመራችሁ ነው! ሲሉን እናዳምጣቸዋለን ብዙውን ጊዜ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ መልስ እንሰጣለን እነሱ የፖለቲካ ጉንፋን ሲይዛቸው እኛንም ክፉኛ ያስነጥሰናል፡ እርግጥ ነው አንዳንድ ጊዜ ፈረሱ ሳይሆን ጋሪው ፈረሱን ይጎትተው የምንልበትም ጊዜ አልታጣም፡ እንዳቅማችን የምንልካት ሳንቲምም የሳንቲሟ ተቀባዮች በምንላቸው መንገድ እንዲሄዱ (ቢቀጥንም ቢሰፋም) ከማሳሰብብም አልፎ ቀጭን ትዕዛዝ ማስተላለፍም ተጀምሯል፡ ለዚህ ሁሉ ገለልተኝነት የማይታይባቸው ሜድያዎች (ፓልቶክ ዌብ ሳይቶችና የሬድዮ ፕሮግራሞች) ተጠያቂዎች ከመሆን አይድኑም፡

ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የስኑምግባር ስምምነት ተፈራረሙ:: ያ ማለት ወያኔን ተቀላቀሉ! አቶ ሰዬ አብርሃና ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ አንድነትን ተቀላቀሉ በመቀላቀላቸውም አንድነትን ሁለተኛ ወይም ተለዋጭ የወያኔ ቡድን አደረጉት፡ እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም የወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚ ሆኑ!!! ወዘተ ትንሽ ትንሽ እውነት ያለው ነገር ባይጠፋም ስም እየጠሩ ማንጓጠጥ መሳደብ እኔ የምደግፈው ተቀደመ ተበላኝ እነ ኃይሉ ሻውል ለሥልጣን ቀረቡ እነሱን ሥልጣን ላይ ከማየት ወያኔ ዝንተ ዓለም ይግዛን የሚሉም ድምጾች እየተሰሙ ነው፡ ኢትዮጵያውያን በጋራ ልንቆም አልቻልንም:: ምን ይሻለናል? በመሰዳደብ ትልቅ ሰውን በማዋረድ ሃገራችንን እንጠቅማለን? እንደ እኔ ያሉ በሀገራቸው ያለው የፖለቲካ ምስቅልቅል ያሳደዳቸው ኢትዮጵያዊ የማይባል አገዛዝ በተንሰራፋበት አስከፊ አገዛዝ የተንገላታን ከዛሬ ነገ የፖለቲካው አስከፊ ዳመና ገልጦ የሰላምና የነጻነት ጸሓይ ይወጣልናል ብለን የምንጠብቅ ተስፋችን ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች እየጨለምብን ነው፡ እናም እኔን ግራ ገባኝ::

በምንኖርባቸው የስደት ሀገሮች ገና ተቀባይነት ያላገኘን ከሞት ባልተናነሰ ሁኔታ በየአረብ አገሮች ስቃይ በማየት ላይ ያሉና ሕይወታቸውም በማለፍ ላይ የሚገኙ እህቶቻችን ተስፋ ሲደበዝዝ ስደት ለምኔ እንዳይባል በሀገራችን የሚጠብቀን ዘረኛ አገዛዝ በተቃዋሚዎች የእርስ በርስ ርኩቻ እድሜው ሲረዝም እየታየን ግራ ተጋብተናል፡ አንድ መሆኑ ቢያቅት እንዴት መቻቻል ያዳግታል? ለትግሉ የበኩላቸውን የትግል አስተዋጽኦ ሲያደርጉ የተሰውትን እህቶች፣ ወንድሞችና እናት አባቶች እንዴት ረሳናቸው? ሌላው ይቅርና በመጪው ምርጫ መሳተፍ ወይም አለመሳተፍ የሚለው ገና በውል አልተቋጨም::

አንዱ የሌላውን ስም ሲያጎድፍ ሌላው ደግሞ አብልጦ ሲለቀልቅ በአንዳቸውም ላይ እምነት እንድናጣ መደረግስ ያለብን ይመስላችኋል? ሰሞኑን በድረ ገጾች ላይ ካነብብኳቸውና እኔን ግራ ካጋቡኝ ነገሮች አንዱና ዋናው በአዲስ አበባ ተደረገ ስለተባለው "ታላቁ ሩጫ"ና ተደመጡ ስለተባሉት መፈክሮች ነገር ነው፡ የማስታውሰውን ያህል በዚያ "የሕዝብ ቁጣ" ተባሉ የተባሉት ሁሉ በአብዛኛው አቶ ኃይሉን የሚያወግዙ ወይዘሪት ብርቱካንን

የሚያሞግሱ አልፎ አልፎም ቢሆን ልደቱ አያሌውን የሚጠቃቅሱ እንጂ በአንዱም ላይ ወያኔን የሚኮንኑ መባላቸውን እንዳቸውም ድረ ገጾች ፍንጭ አልሰጡም:: በእርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ወንጀል ይልቅ የአቶ ኀይሉ መፈራረም ከፍቶበት ነው? እንዴትስ በአንድ ቃል መፈክር ለማሰማት እየዘመሩ ለመሮጥ የጋራ ጊዜ አግኝተው አጡት? ወይስ በብጣሽ ወረቀት እየተደረገ ታድሎ ይሆን? ማን አደለ? የሚሉት ሁሉ እኔን ግራ ያጋባኛል:: ትልቁንና ዋናውን ነገር ጥለን በፖለቲካ ባላንጣዎቻችን ላይ ጥቃቅን ነጥቦች ለማስቆጠር የምንሯሯጥ እየመሰለኝ እኔን ግራ ገባኝ::

ወያኔ 60+ ፓርቲዎችን ፈልፍሎ በአንድ በኩል አንድ ላይ እንዳይቆሙ ከፋፍሏቸዋል: በሌላ በኩል ብቻውን ሮጠ እንዳይባል የፓርቲ ካባ አልብሷቸው በውጪ ደጋፊዎቹም ዘንድ" ዲሞክራቸ" የሚል ስም አስገኝቶለታል: የእነ አቶ ኃይሉ መግባትም ሆነ አለመግባት ለስሙ ይህንን ያህል የሚፈይደው እንደማይኖር የታወቀ ነው: በቀሪው ጊዜ ምን ይደረግ? ኢትዮጵያን ከወያኔ መንጋጋ ለማላቀቅ በሃቅና ኢትዮጵያዊነት ላይ የተመሰረተ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል:: ያ እርምጃ ምን ሊሆን ይገባዋል? የፖለቲካ መሪዎች ከምንላቸውና የቅርብ ደጋፊዎቻቸው የምናገኘው መሰዳደብና ስም መጠፋፋት ከሆነ እኛ ከስደት አቅም እንኳዋን የስደተኛነት እውቅና ያላገኘነው እስቲ ሃሳብ እንለዋወጥ!

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ!

በ e-mail: azebtesfaye@rocketmail.com አስተያየታችሁንም ሆነ ምክራችሁን እቀበላለሁ::